## ምዕራፍ ሁለት

# የስነጽሁፋዊ ሂስ አጭር ታሪክ

- የስነ ጽሑፋዊ ሂስ መቼና የት ተጀመረ?
- በስነ ጽሑፋዊ ሂስ ታሪክ ቀድመው የሚጠቀሱ ሀገራትና ግለሰቦችን ታውቃላችሁ?

ሂስን በዚህ ዘመንና በዚህ ቦታ ተጀመረ ብሎ ቁርጥ ባለ መልኩ መናገር ባይቻልም ከፕሌቶ (428-327 B.C) ጀምሮ ይካሄድ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የመነሻ ዘመኑም ብቻ ሳሆን ቦታውም እንድሁ አወዛጋቢ ነው፡፡ በጥንታዊ ግሪክ ፣በጥንታዊ ቻይናና በአረቢያ ተጀመረ የሚሉ መላምቶች ተንጸባርቀውበታል፡፡ የሂስ ዘመኑን የተለያዩ ምሁራን በተለያዩ የጊዜ እርከኖች ይከፋፍሉታል፡፡ ይሁን እንጅ ዋና ዋና መገለጫዎቹ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡

1. **ጥንታዊ የስነ ጽሑፍ ሂስ** (Classical Literary Criticism)

ይህ ቀዳሚው የስነ ጽሑፋዊ ሂስ ዘመን ነው፡፡ ይህ ዘመን ከ800 B.C ጀምሮ እድሜው ይቆጠራል፡፡ ከዚህ የሂስ ዘመን ጋር ተያይዛ የምትጠቀሰው ጥንታዊ ግርክ ናት፡፡ Criticism የሚለው እሳቤና ቃል በራሱ መነሻው ጥንታዊት ግሪክ ስትሆን kritos ከሚለው የጥንታዊ የግሪክ ቃል ሲሆን Juge (ዳኝነት)ከሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ጋር ትይዩ ነው፡፡ ቃሉ በአንድ ኪነ ጥበባዊ ስራ ላይ ውሳኔ፣ ፍርድ፣መስጠትን ያመላክታል፡፡

በጥንታዊ ግሪክ ከ800 B.C ጀምሮ ሂስ ይደረጋል፡፡ የዘመኑ ዋነኛ መመዘኛ ይዘት ነበር፡፡ እነዚህ የሂስ ጠቋሚዎች ከጥንታዊው ፈላስፋ ፕሌቶ በፊት ጀምሮ በሚትና በሌጀንድ እንድሁም በሆሜር ኤፒክ ግጥሞች ይታወቃል፡፡ ፕሌቶ የምዕራባዊያን የፍልስፍና ምንጭ ተደርጎ

ይወሰዳል፡፡ ስነ ጽሑፍን የፍልስፍናው መግለጫ ብቻ ሳይሆን የፍልስፍናው አንዱ አካል አድርጓል፡፡

ወደ ፕሌቶ ዘመን (428-347 B.C) ስንመጣ ፕሌቶ የጥንታዊ ግሪክ ፈላስፋ ሲሆን ፍልስፍናውን የጀመረው በግጥምና በግጥማዊ ስራዎች ላይ ሂስ በመስጠት ነው፡፡ በሆሜር ስራዎች ላይ ግጥማዊ በሆነ መንገድ ሂስ አድርጓል፡፡

ቀጣዩ የዚህ ዘመን የሂስ ሰው አርስቶትል (384-322 B.C) ነው፡፡ አርስቶትል የፕሌቶ ተማሪ ሲሆን እሱም በፍልስፍናው መልክ ገናና ሆኖ ገፍቷል፡፡ በዚህ የሂስ ዘመን ይዘትን መለኪያ አድርጎ ስነምግባራዊ ሂስ ተሰጥቶበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለስነጽሁፋዊ ሂስ መነሻ የሆኑ መሰረቶች ተጥለውበታል፡፡ እነዚህ መሰረቶች

- ኩረጃ (Imitation )
- አስተማስሎ (Representation)
- ተዝናኖት (Catharsis)
- ማስተማር(Didacticism)

አርስቶትልና ፕሌቶ ኩረጃ የግጥም ዋና መገለጨው እንደሆነ አሳይተዋል፡፡ፕሌቶ ግጥም የግልባጭ ግልባጭ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ማለትም ይህ የምንኖረው አለም ከሌላ ከማናውቀው አለም የጠገለበጠ ነው፡፡ ኪነጥበብ ደግሞ ከምንኖረው አለም እንዳለ የተገለበጠ ነው ብሎ ያምናል፡፡

አርስቶትል በበኩሉ ስነ ጥበብ ኩረጃ እንደሆነ ቢያምንም ኩረጃው ቀጥተኛእና እንዳለ የተወሰደ ሳሆን ፈጠራዎች የታከሉበት፣ምክኒያታዊነት የሚታይበት ጥበብ መሆኑን ያክላል፡፡

ከነ አርስቶትል ቀጥለው በዚህ ዘመን የነበሩት የስነጽሑፍ ሂስ ሰዎች Horane (65-8 B.C) Quantilian ናቸው፡፡ ሃያሲያኑ የስነጽሑፍ ሂሱን ያሳደጉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

2. የመካከለኛው ዘመን የስነ ጽሑፍ ሂስ (5ተኛው -15ተኛው ክ/ዘመን A.D)

የዚህ ዘመን የስነ ጽሑፍ ሂስ በጥንታዊ ዘመን የስነ ጽሑፋዊ ሂስ ተመስርቷል፡፡ የዘመኑ የስነ ጽሑፋዊ ሂስ በዋነኝነት ሐይማኖታዊ ስራዎች ላይ ትኩረት አድርጎ የኩረጃ (Imitation ) ጽ ንሰ ሃሳብን የተከተለ ነበር፡፡ ይህ በኋላ ለመጣው አለማዊ ሂስ መሰረት መሆን ችሏል፡፡ በዘመኑ

የኩረኛ ጽንሰ ሀሳብን ከማቀንቀን በጠጨማሪ ስነ ጽሁፍን በአይነት በአይነቱ መመደብና የስነ ጽሁፍን ቅርጽና መዋቅር መተንተን ተጀምሯል፡፡
ሐይማኖታዊ ቴክስቶችን ከመፍታትና ከመተንተን ጋር ተያይዞ ትዕምርትን (Symbol) መረዳትና መተርጎምም የሂሱ አካል ነበር፡፡

3. **የዘመነ ሕዳሴ የስነ ጽሑፍ ሂስ** (Renaissance Criticism/ 15ተኛው -19ኛው ክ/ዘመን)

የህዳሴ ዘመን ሂስ ልደት ከ1498 A.D ይጀምራል፡፡ በዚህ ዘመን ጥንታዊ የስነ ጽሑፍ ስራዎች እንደገና መታየት ጀምረዋል፡፡ የጥንታዊ ዘመን የስነ ጽሁፍ ስራዎች ወደተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉመዋል፤ተተንትነዋል፤ ጥልቅ ሂስ ተደርጎባቸዋል፡፡ በተለይ የአርስቶትል ስራዎች ይበልጥ ትኩረት ተደርጎባቸዋል፡፡ በዘመኑ ሂስ

- ✓ ከይዘት ብቻ ሳይሆን ከቅርጽ አንጻርም በሰፊው ይደረጋል፡፡
- ✓ የአጻጻፍ ስልት
- ✓ የደራሲው እምነትና አመለካከት

ከመመዘኛዎቹ ናቸው፡፡
በዘመኑ ሂሶች በጋዜጦች ላይ እየታተሙ መውጣታቸው አጠቃላይ በስነጽሁፉና በሂሱ ላይ መነቃቃትን ፈጥሯል፡፡
በዚህ ዘመን በተለይም ለተተዋኝ ጥበቦች አድስ የታዩ የስነጽሁፍ ሂስ ትኩረቶች
ቦታ ድርጊትና ጊዜ የሚሉት ጽንሰ ሀሳቦች ናቸው፡፡

4. **የ19ኘው ክ/ዘመን የስነ ጽሑፋዊ ሂስ** (romantic criticism)

ይህ ዘመን በስነ ጽሑፋዊ ሂስ ላይ አዳድስ አቅጣጫዎች ታይተውበታል፡፡ አጠቃላይ ስነጽሑፉም ቢሆን ጥበባዊነቱ እየጎላ መጥቷል፡፡ በዘመኑ ከታዩ የስነጽሁፋዊ ሂስ አቅጣጫዎች መካከል New Criticism, Romans Formalism, ተጠቃሾች ናቸው፡፡
የዚህ ዘመን የስነ ጽሑፋዊ ሂስ አቅጣጫ ትኩረት ቴክስትን ማዕከል ያደረገ ሆኗል፡፡ በዘመኑ ስነ ጽሑፍን ከደራሲ አንጻር ሂስ ማድረግ አስፈላጊ እንደልሆነና ቴክስት ለሂስ አንኳር ነገር እንደሆነ ተቀንቅኗል፡፡

5. **የ20ኘው ክ/ዘመን የስነ ጽሑፋዊ ሂስ**

ይህ ዘመን ከምንጊዜውም በተለየና በላቀ መልኩ የአለም ነባራዊ ሁኔታን የቀየሩ በርካታ ክስተቶች የተስተናገዱበት ነው፡፡ የኢንዱስትሪ አብዮት ያበበበት፣ ኢምፔሪያሊስም የተስፋፋበት፣

አንደኛውና ሁለተኛው የአለም ጦርነት የተከሰተብትና በዚህ መነሻነት የአለም ሀገራት የሀይል አሰላለፍ ጎራ ተለይቶ የቆመበት ዘመን ነው፡፡ እነዚህ ክስተቶች በስነ ጽሑፋዊ ሂሱም የተለያዩ አተያዮች እንድፈጠሩ ድርሻ  አበርክተዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ዘመን በይነድሲፕሊናዊ የስነ ጽሁፍ ንባብ  እሳቤ ተፈጥሯል ፡፡ ይህ ዘዴ ስነ ጽሑፉንና የሂሱን ጥበብ ወደ ላቀ ደረጃ አሳድጓቸዋል፡፡

**በዘመኑ ከተቀነቀኑ የስነ ጽሑፋዊ ሂስ አይነቶች መካከል፡-**

-ፍካሬ ልቦናዊ ሂስ (psychoanalysis )

-አነስታይ ሂስ (Feminis )

-ቅርጻዊ ሂስ (Formalism)

-መዋቅራዊ ሂስ (structuralism)

ይገኙበታል፡፡